# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የደብረ እንቍዕ ቅድስት ማርያም ወቅዱስ ሩፋኤል ገዳም ሜምፊስ ቴነሲ

# Ethiopian Orthodox Tewahedo Debre Enque Kidist Mariam Kiduse Rufael Gedam Memphis Tennessee

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን።

በደብረ ዕንቊዕ ቅድስት ማርያም ወቅዱስ ሩፋኤል ገዳም

የጽዋዕ ማኅበራት አደረጃጀት የውስጥ ደንብ

መግቢያ

ጽዋዕ፡- ማለት በቁሙ ኩባያ፣ዋንጫ፣የመጠጥ መሣሪያ የሚል ትርጉም አለው። በሌላም በኩል በጽዋ ተቀድቶ የሚሰጥም መጠጥ ጽዋዕ ይባላል። ማኅበር ማለት ደግሞ "ኀብረ" አንድ ሆነ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ነው። ነገር ግን ጽዋዕ የሚለው የግእዝ ግስ ምሥጢራዊ ይዘቱ ሲፈታ "ጸውአ" ወይም ጠራ የሚል ፍቺ አለው። ይህም ማለት የሥላሴን ስም፣ የቅድስት ድንግል ማርያምን ስም፣ የቅዱሳን መላእክትን ስም፣ የጻድቃን ሰማእታትን ስም በመጥራት በስማቸው የሚቀረስ ጠዲቅ የሚቀመስ ውሃ አዘጋጅ ማለት ነው።

በአንድ ላይ የጽዋ ማኅበር ማለት በአንድ ጽዋ ለመጠጣት የሚሰባሰቡ የምእመናን አንድነት ማለት ነው። በጽዋ ማኅበር መሳተፍ በረከትን ያሰጣል (መዝ 3፡8፣ ምሳ10፡7) እንዲሁም በማቴ 10፡42 ላይ እንደተገለጸው ዋጋችን በእግዚአብሔር ዘንድ አይጠፋብንም። የጽዋዕ ማህበር መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ ሥርዓት እንደመሆኑ የራሱ የሆኑ ዓላማዎች አሉት ከነዚህም ውስጥ በማቴ 10፡42 ላይ ካለው፤

1. የበረከት ተካፋይ ለመሆን።
2. ስለ ሃይማኖታችን፤ ስለቤተክርስቲያናችን ለመወያየት
3. ልባዊ ፍቅርን ለማጽናት የሚሉት ይገኙበታል።

ነገር ግን ባለንበት ዘመን በጽዋ ማኅበር ስም እየተመሠረቱ ያሉ ማኅበራት ከእነዚህ አላማዎች ውጭ በሆኑ እኩይ ተግባራት ተሰማርተው ቤተክርስቲያንን የሚያውኩበት ሁኔታ ሲፈጠር ይታያል። ምዕመናንን በማሳሳት ወደ አልሆነ አቅጣጫ የሚወስዱ አንዳንድ የጽዋዕ ማኅበራት በየአጥቢያው መኖራቸውን ዕለት በዕለት የምንታዘበው ነው። በተለይ የሐሰተኛውን መሲህ መምጣት በማፋጠን መንገድ ጠራጊ ሆነው የመጡ ማኅበራት እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል።

በማኅበራዊ ሚዲያዎች ሳይቀር ራሳቸውን እንደ ልዩ መልእክተኛ አድርገው ደካማ ጎኑን በመጠቀም የዋሁ ምእመን ማኅበራቸውን እንዲቀላቀል የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ቀላል የሚባል አይደለም። እንቅስቃሴውም በሀገር ውስጥ፤ በገጠርና በከተማ፣ ከሀገር ውጪም እንዲሁ በአብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ በጽዋዕ ማኅበር ስም ብዙ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

2449 Altruria RD Bartlett TN 38134

እምነት ተከታዮችን እያታለሉ፤ አባላቶቻቸውን የማብዛት ብሎም ሃይማኖታችንን የመፈታተን ሂደቶችን እንዳሉ ልንገነዘብና አካሄዳቸውን ልናጋልጥ ይገባናል።

ከዚሁ ግንዛቤ በመነሳት በደብረ እንቁ ቅድስት ማርያም ወቅዱስ ሩፋኤል ገዳም የሚሰባሰቡ የጽዋዕ ማህበራት ከላይ ካለው የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ውጪ እንዳይወጡ ይህንን ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም ማንኛውም በገዳሙ ውስጥ የሚመሰረት የጽዋ ማኅበር የሚከተሉትን ነጥቦች ማሟላት ይጠበቅበታል።

1. ማንኛውም የጽዋዕ ማህበር የሚቋቋመው በመጀመሪያ ለምን አላማ እንደሚቋቋም የሚገልጽ ማስረጃ በማቅረብ በሰበካ ጉባኤው ፈቃድ አግኝቶና ለጠቅላላ ጉባኤው ቀርቦ ከጸደቀ ብቻ ነው።
2. ማንኛውም የጽዋዕ ማህበር በማህበሩ አባልነት መሳተፍ የሚፈልጉ የቤተክርስቲያኗን ምዕመናንን ሁሉ የመቀበልና በእኩልነት የማስተናገድ ግዴታ አለበት።
3. ማንኛውም የጽዋዕ ማህበር በቋሚነት በማህበሩ ስም ምንም አይነት ገንዘብ መሰብሰብም ሆነ በማህበሩ ስም የባንክ ሂሳብ፣ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲኖረው አይፈቀድም። ነገር ግን ዝክር ለመዘከር በጊዜያዊነት ገንዘብ ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሰበካ ጉባዔው በማሳወቅ ማሰባሰብ የሚቻል ሲሆን ለዝክሩ የሚሆነው ወጭ ከወጣ በኋላ ቀሪው ገንዘብ ወዲያውኑ ለቤተከርስቲያን ገቢ መደረግ ይኖርበታል።
4. በማንኛውም የጽዋዕ ማህበር መረሃ ግብር ጸበል ጸዲቅ ዘክሮ፣ ተምሮ፣ ዘምሮ እና መንፈሳዊ ስብከት ተሰብኮ ከመሄድ ውጭ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የፖለቲካም ሆነ ማንኛውንም የቤተክርስቲያኗን የአስተዳደር ሥራና ምዕመኑን የሚያውኩ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን ፈጽሞ የተከለከለ ነው።
5. የገዳሙ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ማንኛውም የጽዋዕ ማህበር የሐይማኖት ችግር ካለባቸው እና ከሚጠረጠሩ ግለሶቦችም ሆነ ድርጅቶች ጋር ግንኙት እንዳለው ከደረሰበት ማህበሩ ማስተካከያ እንዲያደርግ ምክር ይሰጣል። ከዚህ በኋላ የማህበሩ አቋም የማይስተካከል ሆኖ ሲገኝ፤ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤው ጉዳዩነ ለቁጥጥር ኮሚቴው በማሳለፍ እንዲጣራ የሚያደርግ ሲሆን፤ የማጣራቱ ስራ እስኪጠናቀቅና ለጠቅላላ ጉባኤው ቀርቦ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ የማህበሩን እንቅስቃሴ ሊያግድ ይችላል።
6. ማንኛውም የጽዋዕ ማህበር አባል የቤተክርስቲየን አባል መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ በገዳሙ መተዳሪያ ደንብ መሰረት አስራቱን (ወርሃዊ ክፍያውን) የሚከፍል መሆን ይኖርበታል። የጽዋዕ ማህበሩ አባላቱ ይህንን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የማስተባበር ሃላፊነት ያለበት ሲሆን ይህንን ግዴታቸውን ለመወጣት ፈቃደኛ ያልሆኑትን አባላቱን ከአባልነት ያስወግዳል። ማህበሩ ይህንን ተግባራዊ የማያደርግ ሆኖ ሲገኝ የገዳሙ የሰገካ አስተዳደር ጉባዔው ማህበሩን እሰከማገድ የሚደርስ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

**የደንቡ ተፈጻሚነት፤**

ይህ ደንብ ለጠቅላላ ጉባዔው ቀርቦ ከጸደቀበት እለት ጀምሮ የገዳሙ መተዳደሪያ ደንብ አካል በመሆን አሁን ባሉትም ሆነ ወደፊት በሚመሰረቱ የጽዋ ማኅበራት ሁሉ ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

ሕዳር **2016** ዓ ም